



# ሲያልና ገነት፡

## አንድ ሺህ ለአንድ

በሬቨረንድ ፓርክ ዮንግ ጊዩ
(By Rev. Park, Yong Gyu).
http://www.DivineRevelations.info/Amharic

በ1987 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ሬቨረንድ ፓርክ በከፍተኛ የደም ግፊት ምክንያት ሞቱ። ነገር ግን **በእግዚአብሔር** ጸጋ ህይወታቸው ለ20 ዓመታት ተራዘመ። ሆኖም ግን ለመጀመሪያዎቹ አራት ዓመታት፥ ከነበሩበት ሁኔታ የተነሳ መናገር አይችሉም ነበር። ወደ ህይወት ተመልሰው ሲመጡ 50 ዓመት እድሜያቸው ነበር። በሞታቸው ጊዜ ጌታ ገነትንና ሲያልን አሳይቷቸዋል።



ትዕቢተኛና ትምክህተኛ ከሆናችሁ በራሳችሁ ላይ እርግማንን እንደምታመጡ ልነግራችሁ እወዳለሁ። 5000 አባላት ያሉት ትልቅ ቤተክርስቲያን አለኝ ነገር ግን በትምክህቴ የተነሳ **በእግዚአብሔር** ተመታሁ። አሁን **እግዚአብሔርን** እፈራለሁ። (ያዕቆብ 4:6)

150 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ሀብት ነበረኝ። አምስት የቅንጦት መኪኖችም ነበሩኝ። ነገር ግን ከሞት ገጠመኜ በኋላ ሁሉንም ለሌሎች ሰጠሁት። እባካችሁ ይህን አስታውሱ፥ መዳን ባላችሁ ንብረት አይገኝም ነገር ግን በእምነት ነው። እናም አሁን በሌሎች ቤተክርስቲያናት የምትገኙ ዲያቆናትን፣ ሽማግሌዎችን፣ እናም ሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎችን መጋቢዎቻችሁን (ፓስተሮቻችሁን) በሙሉ ልባችሁ እንድታገለግሉ እለምናችኋለሁ።

በ1987 ዲሴምበር 19 (እ.ኤ.አ)፥ ምሳዬን በልቼ እንደጨረስሁ እረፍት በማድረግ ላይ ሳለሁ፥ ከባድ ህመም ይሰማኝ ጀመር፥ ስሜቱ ልቋቋመው የማልችለው ከመሆኑ የተነሳ እንደምሞት አሰብሁ። ከዛም ራሴን ሳትሁኝ። ከአራት ወራት በኋላ ስነቃ ሰውነቴን ደንዝዞ አገኘሁት፥ እናም ሀኪሜ መሞቴ እንደማይቀር ነገረኝ። ሰውነቴ ስለማይንቀሳቀስ ክፉኛ አባብጦ ነበር። ከሚያሰቅቀው ሁኔታዬ የተነሳ ቤተሰቦቼ ማንም የቤተክርስቲያን አባል እንዲያየኝ አይፈቅዱም ነበር። ኋላም በመጨረሻ ሞትሁኝ።

ልክ ስሞት፥ ሁለት ሰዎች ወደ ክፍሌ ሲገቡ አየሁ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ወደ ክፍሉ የገቡት በግድግዳ ውስጥ ነበር። "ማናችሁ እናንተ!! እንደዛ የምታረጉ ከሆነ ቤቴ ይፈርሳል!!" ብዬ ጮኽኩ። ከዛም አንዱ እንዲህ አለ፥ "እኛ ከሰማይ የመጣን *መላእክት* ነን፥ ከ**እግዚአብሔር** *መንግሥት* ነን።" ከመላእክቶቹ አንጸባራቂ ብርሃን ይፈነጥቃል።



በቀኜ የነበረው *መልአክ* ራሱን አስተዋወቀ "*ለ**ኢየሱስ** በመንግሥቱ ተልዕኮዎችን እፈጽማለሁ። **ኢየሱስ** ጠርቶ ወደ ምድር እንድመጣ አዘዘኝ። አንተን ወደ ገነት እንድወስድህ አዘዘኝ። አንተ ሞተሀል። ነገር ግን ቤተሰቦችህ በብዙ ኀዘን እያለቀሱ ስለሆነ ጥቂት እንድትኖር እድሜ ሊጨምርልህ ወስኗል። ግን ለአሁን ገነትንና ሲያልን ሊያሳይህ ወስኗል። **እርሱ** ያሳይሀል አንተም በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ትመሰክራለህ። በአንተ ምስክርነት ወደ ሲያል የሚወርድ ነፍሳት ቁጥር ቀንሶ ወደ ገነት የሚገቡ ነፍሳት ቁጥር ይጨምር። ይህ የአንተ ተልዕኮ ይሆናል። **እግዚአብሔር** እንዳትዘገይ እንድንነግርህ አዝዞናል። ከዘገየህ፥ ገነትና ሲያልን አትጎበኝም።*"

ከዚያም በግራዬ የነበረው መልአክ እንዲህ አለ፦ "*ከተወለድህበት አፍታ ጀመሮ እስከሞትክባት ቅጽበት ድረስ አብሬህ ነበርሁ።*" በዚያ ሠዓት፥ *መልአኩ* ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝም። አሁን ግን ጠባቂ *መልአኬ* እንደሆነ አወቅሁ። ስለዚህ እንዲህ አልኩኝ፦ "ልሄድ አልችልም! አልሄድም! እኔ መጋቢ ነኝ! ጌታን በእንደዚህ ዓይነት የሰውነት አቋም ላገኘው አልችልም። ላየው የምፈልገው ጤነኛ ሰው ሆኜ ነው።

ከጌታ ዘንድ ከአስተያየት ይልቅ ብዙ ነቀፋዎች እቀበላለሁ። እኔ ትዕቢተኛና ትምክህተኛ ነኝ እናም አሁን የተረገምኩና በሽተኛ ነኝ። እንዴት ነው ገነት ልገባ የምችለው? በጣም ፈርቻለሁ። እባካችሁ ወደ ገነት ተመለሱና ለጌታ እንዲፈውሰኝ ንገሩት። ከዛም ተመልሳችሁ መጥታችሁ በህልም ወደ ገነት ውሰዱኝ። እባካችሁ በእኔ ፋንታ ምህረትን ለምኑልኝ።”

ነገር ግን መላእክቱ የእኔን ክርክር እየሰሙ አልነበረም። ልብሶቹን አወለቁና በገነት ለመልበስ አስቀያሚ እንደሆኑ ነገሩኝ። ከዚያም ነጭ ልብስ አለበሱኝ። (ዘካሪያስ 3፡4)



እጆቼን ያዙኝና ወደ ሰማይ በረርን። በደመናዎች ውስጥ በረርን፥ እናም ወደ ታች ስመለከት ምድርን እያነሰች አየኋት። ከዚያም መጨረሻ ወደሌለው ወርቃማ መንገድ አጠገብ አመጡኝ። አንጸባራቂ የሚያበራ ብርሃን አየሁ፥ በቀጥታ ለማየት በጣም ደማቅ የሆነ። “ብርሃኑ ከየት ነው የሚመጣው?” አልኩኝ። *መላእክቱም “ከገነት ነው፤”* ብለው መለሱልኝ።

“ይገርማል! ግዙፍ ነው!” ብዬ አሰብሁ። ነጫጭ የለበሱ ሰዎች ቀድመውኝ ሲበሩ አየሁ። “ማናቸው?” ብዬ ጠየቅሁ።

*መልአኩም መለሰ፦ “እነዚህ ሁሉን ቻዩን አምላክ በታማኝነት ያገለገሉና በሙሉ ልባቸው የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በመከተል በኢየሱስ የታመኑ ናቸው። በምድር ሰውነታቸው ሞቷል። አሁን እነርሱ ወደ ገነት የሚሄዱ ነፍሳት ናቸው።”*



ሌላኛውም *መልአክ* ቀጠለና፦ *“በገነት አስራሁለት በሮች አሉ። የዳነች ነፍስ ወደ ገነት ስትመጣ ከእነዚህ በአንዱ መግባት ይኖርባታል።”* በደቡብ በር በኩል ቆመን ነበር ነገር ግን ዝግ ነው። እየጠበቅን እያለ፥ *መላእክቱን*፦ “*መላእክት፥*ለምንድ ነው ይህ በር ያልተከፈተው?” ብዬ ጠየቅኋቸው።

*መላእክቱም መለሱ፦ “ምክንያቱም አንተ የገነትን የምስጋና ዝማሬ እየዘመርህ ስላልሆነ ነው።”* (መዝሙር 100፡4)

እኔም ጠየቅሁ፦ “*መላእክት፥* እኔ ትዕቢተኛና ትምክህተኛ ሰው ነበርሁ እናም በዚህ ምክንያት በበሽታ ተረገምሁ። እኔ ምድራዊ የምስጋና መዝሙሮችን በመዘመር እንኳን ጥሩ አይደለሁም። እና ከዚህ በፊት ሰምቼ የማላውቀውን ሰማያዊ ምስጋና እንዴት አድርጌ ነው መዘመር የምችለው?”

*መላእክቱም፦ “ልክ ነህ፥ ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን ራስህን ለምስጋና ማዘጋጀት ይኖርብሀል። አንተ ትዕቢተኛ ሰው ነህ ነገር ግን ለመዘመር ተዘጋጅ።”* ብለው መለሱልኝ። ከዛም *መላእክቱ* መዘመር ጀመሩ፥ እናም እነርሱ ሲዘምሩ እኔም አብሬያቸው መዘመር ጀመርሁ። ለእኔ እንደተፈጥሯዊ ሆነልኝ፥ እናም ወደ ውስጥ ገባን።

የገነት እይታ የማይገለጽ ነው። በምድራዊ ቃላቶቹ ገነትን ልገልጻት አልችልም። እንዲህ አልሁኝ፦ “**ጌታ ሆይ**! በጣም አመሰግንሀለሁ! ምንም እንኳን፥ ትዕቢተኛና ትምክህተኛ በህመም የተረገምሁ ብሆን፥ **አንተ** ግን ልታስጎበኘኝ ወደ ገነት አመጣኸኝ።”

ከዚያም የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰማሁ፦ “*ወዳጄ መጋቢ ፓርክ፥ዮንግ ጊዩ፥እንኳን ደህና መጣህ። ወደዚህ ረዥም ጉዞ አድርገሀል።”* ድምጹ በፍቅርና ርኅራኄ የተሞላ ነበር።

*እያነባሁ መለስሁለት፦ "ጌታ ሆይ፥ ..." መላእክቱ ወዲያው "ለ20 ዓመታት መጋቢ ነበርህ። መጻሕፍትን አታውቅምን? በገነት እንባ የለም። እባክህ አቁመው!"* አለኝ። ማልቀስ እንኳ አልቻልኩም ነበር። (ራዕይ 21፡4)



ከዚያም ጌታ አምስት ጥያቄዎችን ጠየቀኝ።

"***ቃሌን(መጽሐፍ ቅዱስን) በማንበብ ምን ያህል ጊዜ አሳልፈሃል?***
***ምን ያህል መባ ሰጥተሀል?***
***ምን ያህል ጊዜ ለሰዎች ወንጌልን ሰብከሀል?***
***በአግባቡ አስራትን ታወጣ ነበር?***
***በጸሎት ምን ያህል ጊዜ አሳልፈሃል?***"

አምስተኛውን ጥያቄ መመለስ አልቻልኩም። ጌታ ስለአምስተኛው ጥያቄ ወቀሰኝ።

"***የግዙፍ ቤተክርስቲያን መጋቢ ከሆንህ ጀምሮ፥ በጸሎት በጣም ሰነፍ ሆነሀል። በሥራ መወጠር ለእኔ እንደምክንያት አይሆንም!***" በኋላም ስለዚህ ንስሐ መግባት ነበረብኝ። "***መላእክቱ በገነትና በሲዖል ብዙ ቦታዎችን ያሳዩሀል። እንደምትፈልገው ያህል ዙሪያውን ተመልከት። በገነትና በሲዖል ብዙ ቦታዎችን ከጎበኘህ በኋላ ትሄዳለህ።***" ነገር ግን ጌታ መልኩን እንዳይ አልፈቀደልኝም።

*መላእክቱ* በመጀመሪያ በገነት ሦስት ቦታዎች ወሰዱኝ።
በመጀመሪያው ቦታ፥ በጋራ የሚኖሩ ሕፃናት ልጆችን አየሁ።
ሁለተኛው ቦታ ደግሞ አዋቂዎች የሚኖሩበት ነበር።
ሦስተኛው ደግሞ እንደምንም ወደ ገነት የገቡ ነፍሳት ያሉበት ቦታ ነበር፥ ምንም እንኳ ገነት ቢገቡም የገቡት ግን አንገት በሚያስደፋ ሁኔታ ነው። (ከሌሎች ምስክርነቶች፦ ሦስተኛው ቦታ በገነት፥ የዳኑ ነገር ግን በህይወታቸው ምንም ዓይነት ፍሬ የሌላቸው፣ እንዲሁ ጊዜያቸውን ያሳለፉ፣ ቁጥብ የጸሎት ጊዜ፣ ከቃሉ ጋር ብዙ ጊዜ የማያሳልፉ፣ ከላይ እንዳለው አምስቱ ጥያቄዎች ዓይነት መልስ የሌላቸው ... የሚኖሩበት ስፍራ ነው። 1ቆሮ.3:15 *የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።*)



ብዙ ሰዎች ሕፃናቶቹ ልጆች እድሜያቸው ምን ያህል እንደሆነ ጠይቀውኛል። የመዋእለ ሕፃናት ዓይነት ልጆች ይመስላሉ። በጾታ እንደምናውቃቸው ሕፃናት ዓይነት እንደወንድም እንደ ሴትም አይደሉም። እያንዳንዱ ሕፃን አብረዋቸው የሚሆኑ የሕፃን *መላእክት* አሏቸው።

በገነት አብዛኞቹ ነፍሳት የራሳቸው ቤት አላቸው። (ዮሐንስ 14፡2) ሆኖም ግን፥ ሌሎች ቤት የሌላቸው ደግሞ አሉ። ይህን በኋላ አብራራዋለሁ፥ ልጆቹም የራሳቸው ቤት የላቸውም። "ልጆቹም እኮ ነፍሳት ናቸው፥ ለምንድ ነው የራሳቸው ቤት የሌላቸው?" ብዬ ጠየቅሁ።

*መልአኩም መለሰ፦ "በምድር ያሉ ሰዎች ቤታቸውን ለመሥራት እቃ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ፥እኛም በገነት ያለነው ለመገንባት እቃዎች ያስፈልጉናል። አንድ ሰው ቤተክርስቲያንና ሌሎችን ለጌታ ታማኝ ሆኖ ሲያገለግል፥ እነዚያ ሥራዎቹ በሰማይ ለአንድ ሰው ቤትን ለመሥራት አቅራቦቶች ይሆናሉ። እቃዎች ሲቀርቡ፥ለቅዱሳኑ የተዛገጁት መላእክቶች ቤት ለመገንባት ወደ ሥራ ይሄዳሉ። በሌላ አገላለጽ፥ ሽልማታቸውን (አቅርቦታቸውን) ለመቀበል ጊዜ አልነበራቸውም። ለዚህ ነው (ሕፃናቶች) ቤት የሌላቸው።"*

ጥያቄዎቼን ቀጠልሁ፥"ለቤቴ ብዙ እቃዎችን ለማቅረብ በምድር ላይ ምን ማድረግ አለብኝ?"

*መላእክቱም መለሱ፦ "አንድ ሰው ለግንባታ እቃዎችን ለማቅረብ ሰባት ነገሮችን ማድረግ ይጠበቅበታል።*



*የመጀመሪያው፥ያጠራቀሙት የእግዚአብሔር የአምልኮና የምስጋና ጊዜ ነው፤*
*ሁለተኛው፥መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ያሳለፉት ጊዜ፤*

*ሦስተኛው፥ በጸሎት ያሳለፉት ጊዜ፣*
*አራተኛው፥ ሰዎችን ወንጌል በመስበክ ያሳለፉት ጊዜ፣*
*አምስተኛው፥ ለ**ጌታ** የሚሰጥ መባ፣*
*ስድስተኛው፥ በመታዘዝ ለ**እግዚአብሔር** የሰጡት አስራት፣*
*በመጨረሻም፥ በማንኛውም መንገድ ቤተክርስቲያንን በማገልገል ያሳለፉት ጊዜ።*
*አንድ ሰው ለሰማያዊ ቤታቸው አቅራቦቶችን ሊያጠራቅምባቸው የሚችልባቸው ሥራዎች እነዚህ ናቸው።*
*አንድ ሰው በእነዚህ ጉዳዮች ከነደለ ቤቱን ለመሥራት ምንም ዓይነት አቅርቦት አይኖራቸውም።*

በገነት ቤት የሌላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። አብዛኞቹ ቤት የሌላቸው መጋቢዎች፣ ዲያቆናት፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ወዘተ. ናቸው። በመገረም "ታዲያ ልጆቹ የት ነው የሚኖሩት?" ብዬ ጠየቅሁ።



*መላእክቱም መለሱ፦ "እዚህ ነው የሚኖሩት።"* ዙሪያውን ስመለከት፥ በአበቦች መስክ ውስጥ ተሰብስበዋል። የአበቦች መስክ እጅግ የሚያምርና መአዛው በዚህ ምድር ፈጽሞ የሌለ ነው። እይታው በቃላት ልገልጸው ከምችለው በላይ ነው።

ሁለተኛው ስፍራ ለታማኝ አዋቂዎች ነበር። በመዳንና በሽልማት መካከል ልዩነት አለ። ይህ ቦታ ብዙ ቤቶች አሉት። ቤቶቹ በሚያማምሩ እንቁዎችና ብርቅዬ ድንጋዮች የተሠሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ቤቶች ርዝመታቸው በምድር ላይ ረዣዥም የሚባሉትን ሕንፃዎች ያክላል። በመድር ሲኖሩ ጌታን በታማኝነት ያገለገሉት ሰዎች ቤታቸው በእንቁዎችና በብርቅዬ ድንጋዮች ተሠርቷል። በዚህ የተለየ ቦታ ያሉ ሰዎች፥ ከ20 እስከ 30 ዓመት እድሜ ያላቸው ይመስላሉ። ከጾታ አንጻር ወንድም ሆነ ሴት የለም። የታመመ፣ ያረጀም ሆነ አካል ጉዳተኛ የለም።



የሆነ ጊዜ የማውቀው ኦ፥ ኢም ምዩንግ የሚባል ሽማግሌ ነበረ። በ65 ዓመት እድሜው ነበር የሞተው። በጣም አጭር ሰው ነበር፥ የ2ኛ ክፍል ተማሪ ያህል ነበር ርዝማኔው። ሪኬትስ በተባለ አልፎ አልፎ በሚከሰት በሽታ ተጠቅተው ነበር። (ሪኬትስ፡ በሕፃንነት ጊዜ በሚከሰት የቫይታሚን ዲ ና የፀሐይ እጥረት የሚመጣ በሽታ ነው።) ሆኖም ግን፥ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ከተነሳ፥ ዶክትሬት አለው። ብዙ ጥቅሶችን (ማብራሪያዎችን) ጽፈዋል። በገነት አገኘሁት፥ እናም በዚያ ረዥምና የሚያምር ሰው ነበር። ምንም በሽታ የሌለበት ጤነኛ ነበር። ገነት በጣም የሚገርም ቦታ ነው!! በመጠባበቆች ተሞልቼ ነበር! የተወደዳችሁ ሰዎች ሆይ እባካችሁ የምላችሁን እመኑኝ!

ሦስተኛው ቦታ አንገት በሚያስደፋ ሁኔታ ለዳኑ ሰዎች ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 3:15) ይህ ልዩ ቦታ በስፋቱ እጅግ ግዙፍ ነበር፥ ከመጀመሪያው ስፍራ በጣም ይሰፋል፥ ማለትም ቤቶቹ በእንቁና በብርቅዬ ድንጋዮች ከተሠሩበት። ወደዚህ ስፍራ ወርቃማ ሰረገላን እየጋለብሁ በከፍተኛ ፍጥነት ደረስሁ። በገነት ካየኋቸው የተዋቡ በታዎች በጣም ሩቅ ነበር።

*መላእክቱን ጠየቅኋቸው* "ትልቅ ምድረበዳና ሜዳ አያለሁ፣ ለምንድ ነው ቤቶችን የማላየው?" *መልአኩም መለሰ፦ "እያየህ ያለኸው ቤቶችን ነው።"*



ግዙፍ ሰፊ የተነጠፉ ቤቶችን አየሁ፥ ረዥም የዶሮ መፈልፈያ ወይም መጋዘኖችን አስታወሰኝ። እነዚህ ቤቶች የተዋቡ አልነበሩም፥ ይልቁንም አስቀያሚዎች ነበሩ። እነዚህ ቤቶችና መንደሮች አንገት

በሚያስደፋ ሁኔታ ለዳኑ ነፍሳት ናቸው። በጣም ብዙ አሮጌ የሚመስሉ ቤቶች ነበሩ። ይህ መንደር የተሸለሙ ነፍሳት ከሚኖሩበት ብዙ እጥፍ ይሰፋል።

*መልአኩ "ሁለቱ ትልልቅ ቤቶች ይታዩሃል፥ አንዱ በቀኝህ አንዱ ደግሞ በግራህ?"* ብሎ ጠየቀኝ። እኔም "አዎ፥ ይታዩኛል" ብዬ መለስሁ።

*መልአኩ* እነዚህን ቤቶች በተለየ ሁኔታ ሊያሳየኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ። እንዲህም አለኝ፦ *"በቀኝ በኩል ያለው በምድር መጋቢዎች ለነበሩ ነው። በግራ በኩል ደግሞ ያለው በምድር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ለነበሩ ነው።"* ወደ ሁለቱ ቤቶች ፊትለፊት ስንደርስ፥ እጅግ ግዙፍ እንደሆኑ አስተዋልሁ። አገጬ ተንጠለጠለ። በሩን ከፍተን ስንገባ፥ መጀመሪያ የመጣልኝ፥ 'የዶሮ ቆጥ' ነበር። ነገር ግን በሺዎች ከሚቆጠሩ ዶሮዎች ፈንታ የሰዎችን ነፍሳት አየሁ። *መላእክቱ* በደንብ ትኩረት ሰጥቼ እንድመለከት ነገሩኝ ምክንያቱ ደግሞ ከታሪክ የማስታውሳቸው ታዋቂ መጋቢዎች ስለሚኖሩ ነው። እውነት ነው ብዙ ከታሪክ የማስታውሳቸውን ታዋቂ መጋቢዎች አየሁ። በተለይ ደግሞ አንዱን መጋቢ ለይቼ *መልአኩን* ጠየቅሁት፥ "ያን ኮሪያዊ መጋቢ አውቀዋለሁ! ምን ያህል ታዋቂ እንደነበረና ለጌታ የሠራውን ሥራ አውቃለሁ። ለምንድ ነው እዚህ ያለው? አልገባኝም።"

*መላእክቱም መለሱ፥ "ለቤቱ ምንም ዓይነት መሣሪያ አላቀረበም። ለዛ ነው በዚህ ያለው።"*



በመጓጓት ጠየቅሁ፥ "ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለምንድ ነው ምንም መሣሪያ የሌለው?" *መልአኩም "መጋቢ እያለ የመጋቢነትን ሥራ በሚሠራበት ጊዜ፥ በሰዎች መሞካሸትን ይወድ ነበር። መከበርን ይወድ ነበር። ሊያገለግሉት ይወድ ነበር። በእርሱ በኩል የሆነ ምንም የተከፈለ ዋጋ የለም።"* ብሎ መለሰልኝ። ይህ መጋቢ እጅግ የተከበረና በኮሪያ ክርስትና ታሪክ እንደ አርአያ የሚታይ ነበር። ሆኖም ግን ምንም ሽልማት አልነበረውም!!

እናንተ መጋቢዎች፥ እባካችሁ አድምጡኝ! ሰዎችን ከእሁድ አገልግሎት ባለፈ ልትመሯቸው ያስፈልጋል። በቤታቸው ልትጎበኟቸው ያስፈልጋል። ድሀውን፣ አካል ጉዳተኞችንና አዛውንቶችን ልትንከባከቡ ያስፈልጋችኋል። ምንም መስዋዕትነትን ያልከፈሉና መወደድንና መከበርን የሚፈልጉ መጋቢዎች በገነት ምንም ትርፍ (ሽልማት) የላቸውም። (የማቴዎስ ወንጌል 23፡5-12)

በገነት ይህንን ራእይ ተመልክቼ ወደ ምድር ከተመለስሁ በኋላ፥ አምስት የቅንጦት መኪናዎቼን ጨምሮ ያለኝን ንብረት ሁሉ አሳልፌ ሰጠሁ። ህይወታችን ለቅጽበት ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ አማካይ እድሜ ከ70-80 ዓመት ነው። ሆኖም ግን **እግዚአብሔር** ብቻ ነው ሰው መቼ እንደሚሞት የሚያውቀው። ማንም ሰው ከ70 ወይም 80 ዓመት በፊት ሊሞት ይችላል። ልብሶቼን ጨምሮ ያለኝን ሁሉ አሳልፌ ሰጠሁ። ያየኋቸው ሰዎች መዳንን የተቀበሉት በእፍረት ነው። መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናት፣ እናም ተራ አማኞች። በእነዚህ የተዘረጉ ያረጁ ቤቶች ውስጥ ብዙ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ነበሩ። እርግጥ ነው ከሲያል በብዙ እጥፍ ይሻላል። ሆኖም ግን፥ ሰው ለምን በዚህ መልኩ ወደ ገነት መግባት ይፈልጋል? በዚህ በሚያሳፍረው ቦታ መሆን አልፈልግም። ልብሳቸው ሁላ አሮጌ ነበር።

ክርስቲያኖች የተዋቡ ቤቶችን ለማግኘት የሚጠበቅባቸው ምንድ ነው? በመጀመሪያ፥ የምንችለውን ያህል ለብዙ ሰዎች ወንጌል መስበክ ይኖርብናል። እንዴት ነው የምንሰብከው? *መልአኩ* እንዲህ አለኝ፦ *"**ጌታን** የማያውቅ አንድ የማያምን ሰው አለ ብለህ አስብ። ልክ ያንን ሰው ለመስበክ ባሰብክበት ቅጽበት የግንባታ እቃዎችህ ይቀርባሉ። ለመዳናቸው ያለማቋረጥ ስትጸልይ ብዙ የግንባታ እቃዎች ይቀርባሉ። እነርሱን መከታተል ያስፈልግሃል፥ እነርሱን መጎብኘትና በቀጣይነት መስበክ። ይህ ብዙ እቃዎችን በቤትህ ላይ ይጨምራል። አንድ ሰው ጥሩ ልብስ ስለሌለኝ ቤተክርስቲያን መምጣት አልችልም ካለ(ች)፥ እናንተ ልትሰጧቸው ይገባል። አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የለኝም*




*ካለ(ች)፥ ልታቀርቡላቸው ይገባል። አንድ ሰው የንባብ መነጽር የለኝም ካለ(ች)፥ ልታቀርቡላቸው የገባል። ይህ(ች) ሰው ወደ ጌታ እንዲመጣ የምትችሉትን ሁሉ ማድረግ ይኖርባችኋል። በምርጥ ቤቶች የሚኖሩት ብዙ ጊዜ ወንጌልን የሰበኩ ናቸው።”*

ከዚያም መልአኩ በተዋቡ ቤቶች የሚኖሩ ቅዱሳን ወዳሉበት ቦታ ወሰደኝ። ይህ ብዙ ወንጌልን የሰበኩ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። የገነት መናህሪያ (መሀል ከተማ) ነው የሚመስለው።

በክርስትና ታሪክ፥ በጣም ትልቁና እጅግ የተዋበ ቤት ያላቸው አራት ሰዎች አሉ። መልአኩ የአሜሪካዊው ሰባኪ ዲ.ኤል. ሙዲ፣ የብሪቲሹ መጋቢ ጆን ዌዝሊ፣ ጣልያናዊ ሰባኪ፣ እናም ኮሪያዊው ሰባኪ መጋቢ ቾኢ፥ ጉንግ ቤት አሳየኝ። እነዚህ አራቱ ሰዎች በገነት ረዥሙ ቤት አላቸው። እነዚህ ሰዎች እድሜያቸውን ሙሉ እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ሰዎችን በመስበክ (የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል) አሳልፈዋል። (American evangelist D.L. Moody, British Pastor John Wesley, an Italian evangelist, and Korean Evangelist Pastor Choi, Gun Nung)

ከኮሪያውያን አማኞች ውስጥ፥ ረዥም ቤት የነበረው ተራ አማኝ ነበር። ይህ አማኝ በንብረቱ ሁሉ ብዙ የቤተክርስቲያን ሕንጻዎችን ገንብቷል። ሦስት ሺህ ማዳበሪያ ሩዝ ለድሆች መጽውቷል። ብዙ መጋቢዎችንና የቤተክርስቲያን መሪዎችን በስውር በገንዘቡ ረድቷል። ብዙ ተማሪዎችን የስነ-መለኮት (ቲዎሎጂ) ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ በክፍያ ረድቷል። እንዲሁም 65 ዓመት የሆነውን መጋቢ ወስዶ በቤቱ በሚገባ ተንከባክቦታል። የገዛ ቤተክርስቲያኑ አባረውት ነበር።



*“የግንባታ እቃዎች እየመጡ ነው!”* ብሎ አንድ መልአክ ጮኸ። በአጠገቤ የነበረውን መልአክ ስለእቃዎቹ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት፥ እርሱም *“እነዚህ እቃዎች በአንድ ትንሽ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለምትገኝ ዲያቆን ነው። ስለእውነቱ፥ በየቀኑ ነው አቅርቦትን የምትቀበለው። ምንም እንኳ ደሀ ብትሆን፥ በየቀኑ በማለዳ አገልግሎቶች ላይ በጊዜ ትገኛለች። በየቀኑ ለ87 የቤተክርስቲያን አባላት በየቀኑ ትጸልያለች። ጸልያ ስትጨርስ ቤተክርስቲያኑን ታጸዳለች።”*

ሌላ መልአክ ሲጮህ ሰማሁ፥ *“ልዩ አቅርቦት! የዲያቆኗ ልጅ ያላትን ጥቂት ገንዘብ ለእናቷ ሰጠች። ሆኖም ግን፥ ዲያቆኗ ለራሷ አላዋለችውም፤ አምስት እንቁላልና ሁለት ጥንድ ካልሲዎችን ገዝታ ለቤተክርስቲያኑ መጋቢ ሰጠች። ምንም እንኳ ስጦታው ትንሽ ቢሆንም ለእለቱ ያላትን ጥቂት ነገር ሰጥታለች። ይህ በገነት ለሚገኘው ቤቷ ልዩ አቅርቦት ሆነ።”*

ሁለተኛው፥ ረዥም ቤት ያላቸው አቢያተ ክርስቲያናትን የገነቡና ለ**እግዚአብሔር** መንግሥት አገልግሎት የተለያዩ ሕንጻዎችን ባላቸው ሀብትና ንብረት የገነቡ ናቸው።



በገነት፥ ቾኢ (Choi) የሚባል ሽማግሌም ተዋውቄ ነበር። በገነት ከሚገኙት ኮሪያውያን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት፥ በጣም የተዋበ ቤት አለው። ቤቱ በኮሪያ ከሚገኙ ረዣዥም ሕንጻዎች ሁሉ ረዥም ነው። ቾኢ በሀብቱ ብዙ ቤተክርስቲያኖችን ገንብቷል።

*መልአኩን* “የእኔስ ቤት? እየተገነባ ነው?” ብዬ ጠየቅሁት። *መልአኩም፥ “ያውና እዛ ጋር!”* አለኝ። ነገር ግን ገና በመሠረት ደረጃ ያለ ቦታ ነው የሚመስለው። ጮኽኩኝ “እንዴት እንዲህ ታደርጉብኛላችሁ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንዴት ቤቴ ገና በግንባታ ደረጃ ሊሆን ይችላል? ከኮሪያ ጦርነት ከተረፍኩ በኋላ፥ ያለኝን አንድ ቤት ሸጬ ቤተክርስቲያን ገነባሁ። ይህ ቤተክርስቲያን በሂደት ወደ አምስት ሺህ አባላት አደገ። በመንፈስ ቅዱስ ተመርቼ ብዙ መጽሐፍትን ጽፌአለሁ። አንዱ መጽሐፍ ምርጥ የተሸጠ ሆኗል። ከመጽሐፍቱ በመቀጠል፥ የክርስቲያን ትምህርት ቤቶችን ገንብቻለሁ። ትምህርት ቤቱ 240 መጋቢዎችን አፍርቷል። ዲን በነበርኩበት ጊዜ፥ ከ400 በላይ

ለሚሆኑ ተማሪዎች ከ400 በላይ ነፃ የትምህርት እድል ሰጥቻለሁ። ለመበለቶች (ባላቸው ለሞተባቸው) የሚኖሩበት ቤቶች ሠርቼላቸዋለሁ። ይህ ሁሉ ብዙ ገንዘብን ይጠይቃል። ታዲያ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንዴት ቤቴ ገና በመሠረት ደረጃ ይሆናል? በጣም ተናድጃለሁ!"

*መልአኩም* በቁጣ *መለሰልኝ፥ "በገነት በእንደዚህ ያለ የተዋበ ቤት ልትኖር አይገባህም ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በሰዎች ስትሞካሽ ነበር። አንድ መልካም ነገር በገነባህ ወይም በሠራህ ቁጥር፥ በሰዎች ትወደስ ነበር። በዓለማዊ ዜና ማሰራጫዎች ሁሉ ትከበር ነበር። ስለዚህ፥ ሥራህ ሁሉ በሥጋ ነበር።"* ([ማቴዎስ 6፡1](#))

ገና በግንባታ ደረጃ ያለውን ቤቴን አየሁ። በሌሎች ሦስት ቤቶች መካከል ነበር። ገና ሦስት ፎቆች ብቻ



ናቸው ያሉት። ቤቱ በምድር ቤትና በመጀመሪያው ፎቅ ላይ ብዙ ትናንሽ ክፍሎች አሉት። *መልአኩን* "እንደዚህ ትናንሽ ክፍሎች የኖሩኝ ለምንድ ነው?" ብዬ ጠየቅሁት። *መልአኩም መለሶ "ክፍሎቹ ለወንዶችና ለሴቶች ልጆችህ ነው።"* አለኝ።

"አራት ልጆች ብቻ እኮ ነው ያለኝ" ብዬ መለስሁ። *መልአኩም መለሰ "አይደለም፥ ለምድራዊ ልጆችህ አይደለም፥ ስለሰበክላቸውና ስለዳኑት ለእነርሱ ነው።"* ወደድሁት! እናም ጠየቅሁኝ "የእኔ ዋና መኝታ ቤቴ የታለ?" *መልአኩም* ጣሪያው ላይ እንደሆነ ነገረኝ። ያ አሳሰበኝ። ክፍሉ ራሱ አላለቀም። በንዴት ድምጽ "በጣም ትንሽ ነው! እንዴት ነው የእኔን ክፍል መጨረስ አስቸጋሪ የሚሆነው?" አልሁ። *መልአኩም መለሰ "ገና አልሞትህም እኮ። ቤትህንም ሆነ ክፍልህን መጨረስ አንችልም ምክንያቱም ተጨማሪ እቃዎች ይምጡ አይምጡ አናውቅም። ገባህ?"*



ወደ ክፍሌ ስንገባ፥ በግርግዳዬ ላይ ሁለት ሰርተፊኬቶች ተሰቅለው አየሁ፥ ስለዚህም ለማየት ሄድሁ። የመጀመሪያው በ18 ዓመቴ በሕፃናት ማሳደጊያ ስለነበርሁበት ይገልጻል። በገና እለት፥ ከጠዋት የቤተክርስቲያን አገልግሎት እየተመለስሁ ነበር። አንድ ሽማግሌ ሰው መንገድ ላይ በብርድ ሲንቀጠቀጥ አየሁ። ጃኬቴን አወለቅሁና ሰጠሁት። ያ ምግባር በገነት ሽልማት አሰጥቶኛል። ሁለተኛውም ሰርተፊኬት ስለተመሳሳይ ነገር ያወራል ሆኖም ግን ባለኝ ጥቂት ገንዘብ ለአንድ አዛውንት ዳቦ ስለገዛሁላቸው ነው። ጉዳዩ መጠኑ አይደለም። ምግባሩ በእውነተኛ እምነት መደረግ ይኖርበታል። የገንዘቡ መጠን ምንም ለውጥ የለውም።




ያን ቦታ ትተን ተመልሰን ወጣን። በጉዞ ወቅት፥ አንደኛው *መልአክ* ጠየቀኝ *"አዝነሃል? የሚያምር ቤት እንዴት ሊገነባልህ እንደሚችል እነግርሀለሁ። ጌታ፥ ወደ ምድር ስትመለስ፥ እንደተመለከትኸው ስለ ገነትና ሲዖል መናገር ይኖርብሀል ብሎሀል። ሁለተኛው፥ ጌታ አሮጊት መጋቢዎችን እና ሰባኪያንን ሰብስበህ የሚኖሩበትን ቤት እንድትሠራላቸው ይፈልጋል። እነዚህን ነገሮች በሀቀኝነትና በእምነት ካደረግሀቸው፥ የሚያምር ቤት ይኖርሀል።"*

## ሲዖል

ሁለቱ *መላእክት* ወደ ሲዖል ወሰዱኝ። እንዲህም አሉኝ፥ *"አሁን ሲዖልን ትጎበኛለህ።"* የሲዖልን አስከፊነት ልታስቡት ራሱ አትችሉም። ጩኸቴን ቀጠልሁ፥ "በጣም ትልቅ ነው! በጣም ትልቅ ነው!" ይህ ነው የተረገሙና የዘላለም ፍርድ የተቀበሉ ነፍሶች የሚሆኑበት። ሲዖል ከምድር ብዙ ሺህ ጊዜ ግዙፍ እንደሆነ ነው የሚመስለው። ግማሹ የሲዖል ክፍል ቀይ ቀለም ሲኖረው ግማሹ ክፍል ደግሞ ድቅድቅ ጨለማ ጥቁር ነው። *መላእክቱን* "ይህ ክፍል ለምን ቀይ ሆነ?" ብዬ ጠየቅኋቸው።

*መላእክቱም መለሱ፥ "አታውቅም እንዴ? ይህ የሚነድ ድኝ (ሰልፈር) ነው። ሌላኛው ግማሽ ጨለማ ነው። ሰዎች ኃጢአትን ሲሠሩና ወደዚህ ሲወድቁ ከሁለቱም ወገን ይሰቃያሉ። ...በምድር ብዙ ቤተክርስቲያኖች አሉ እናም አብዛኞቹ ቤተክርስቲያኖች በሰዎች የተሞሉ ናቸው። ሆኖም ግን፥ አብዛኞቹ የእውነት ክርስቲያኖች አይደሉም። ነገር ግን የቤተክርስቲያን ተካፋይ ብቻ ናቸው። እውነተኞች ቤተክርስቲያኖች በገነትና በሲዖል አጥብቀው ያምናሉ። በሲዖልና በገነት አጥብቀው ባለማመናቸው ምክንያት የአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ህይወት በድብልቅልቅ ውስጥ ነው። አንድ ነፍስ ወደ ገነት ስትገባ፥ አንድ ሺህ የተረገሙ ነፍሳት ወደ ሲዖል ይገባሉ። የገነትና የሲዖል ንጽጽር 1 ለ 1000 ነው።"* (ማቴዎስ 7:14)



የ"ፕሬዝቢተሪያን" መጋቢና በደምብ የታወቅሁ ተናጋሪ ነኝ። በኮሪያ ውስጥ ካሉ ታላላቅ የስነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች ከአንዱ ተመርቄያለው። አንዳቸውንም የገነትና የሲዖል ታሪኮች አምኜባቸው አላውቅም። አሁን ግን፥ ለሌሎች ለመመስከር ከሚጽፉት አንዱ ነኝ። ምንም እንኳ ክርስቲያን እንደሆናችሁ ብታምኑም፥ እንደ አጋንንት ፈቃድ ህይወታችሁን ከኖራችሁ፥ መጨረሻችሁ ሲዖል ነው!

ያየሁት የመጀመሪያው ስፍራ የሚነድ ድኝ ያለበትን ቦታ ነበር። የሲዖል እሳቶች ምን ያህል እንደሚሞቁ ልትገምቱት አትችሉም። ያን ከባድ ግለት ማንም ሊቋቋመው አይችልም።

በሲዖል ያሉ ሰዎች ሦስት ነጥቦችን ይናገራሉ።
የመጀመሪያው፥ በጣም ሞቃት ከመሆኑ የተነሳ እየሞቱ እንዳሉ ይሰማቸዋል። (ሉቃስ 16:24)
ሁለተኛው፥ በጣም ከመጠማታቸው የተነሳ እየሞቱ እንዳሉ ይሰማቸዋል።
ሦስተኛው፥ ብዙዎች ውኃ ሲጠይቁ ትሰማላችሁ። (ዘካሪያስ 9:11)

ዘላለማዊ ነው! ብዙ ሰዎች በ**ክርስቶስ** ነፃ ወጥተናል ብለው ራሳቸው እንደ ፈቀዱ ይኖራሉ። *መላእክቱን* "በዚህ ያሉት ሰዎች፥ ጥፋታቸው ምንድ ነው?" ብዬ ጠየቅኋቸው። *መልአኩም* መለሰ *"የመጀመሪያው ምድብ የማያምኑ ናቸው።"* ለገዛ ቤተሰቦቻቸው ወንጌልን ያልሰበኩ ንስሐ ሊገቡ ይገባል!



*መልአኩም* ቀጠለ፥ *"ሁለተኛው ምድብ በ**ክርስቶስ** የሚያምኑ ናቸው፥ ነገር ግን ስለኃጢአታቸው ንስሐ አልገቡም።"* ከኃጢአታችን ልንመለስና ለ**ጌታ** ልንናዘዝ ይገባል። ፈጽሞ ኃጢአት መሥራት የለብንም። ዝም ብሎ የከንፈር አገልግሎት ብቻ መስጠት ንስሐ አይደለም። በተሰበረና በፍጹም ልቦና ንስሐ ልንገባ ያስፈልጋል!

## ክርስቲያኖች በሲዖል

ከዚያም፥ ብዙ መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎችና ዲያቆናትን በሲዖል አየሁ። *መልአኩንም* ጠየቅሁት፥ "አውቃቸዋለሁ። በምድር **እግዚአብሔርን** በታማኝነት አገልግለዋል። የሆነ ጊዜ ነው የሞቱት። ሁላችንም በገነት ከ**እግዚአብሔር** ጋር እንደሆኑ ነው ያሰብነው። እናም አሁን፥ ያቃጥላል! እያሉ በሲዖል ይጮኻሉ፥ ለምንድ ነው በዚህ ያሉት?" በጣም ብዙ መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና ብዙ ተራ አማኞች በዚያ ነበሩ።

*መልአኩም መለሰ፥ "መጋቢ ፓርክ ዮንግ ጊዩ፥ አንድ ሰው እውነተኛ የ**ክርስቶስ** ተከታይ መስሎ በውጪ ሊታይ ይችላል ነገር ግን ውስጡን **እግዚአብሔር** ብቻ ነው የሚያውቀው።*

**እሁድን ቅዱስ አድርገው አልጠበቁም። ይልቁንም፥ በእሁድ ገንዘብ ማግኘትን ይወዱ ነበር።** (ኤርሚያስ 17:27)

ብዙ ዲያቆናትና ሽማግሌዎች የመጋቢዎቻቸውን አገልግሎት አቃልለዋል። (መዝሙር 105፥15፤ ዘኍልቁ 12፥8-9)



**በአግባቡ አስራት አላወጡም።** (ሚልኪያስ 3፥9)

**አልጸለዩም።**

**ፈጽሞ ለሰዎች ወንጌልን ሰብከው አያውቁም።** (ሕዝቅኤል 33፥6)

**ብዙዎቹ እነዚህ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት መጋቢዎቻቸውን አስመርረዋል እናም ያለስልጣናቸው ይሄዱ ነበር። በመጋቢዎቹ ግዴታና ሥራ ውስጥ ጣልቃ ይገቡ ነበር።** (ዘኍልቁ 16)

በሞት አልጋቸው ላይ፥ መልካም ሥራ እንደ ሠሩ ስላሰቡ ስለእነዚህ ነገሮች ንስሐ አልገቡም። ለዚህ ነው ወደ ሲያል እሳት የተጣሉት።"

ከዚያም የመጀመሪያዎችን ክርስቲያኖች በኮሪያ ውስጥ ያስገደሉትን አንድ ንጉሥና ልዑል አየሁ። ይህ ንጉሥና ልዑሉ ከመጀመሪያዎቹ ኮሪያውያን አማኞች ውስጥ ብዙዎቹን አስቀልተዋቸዋል። በመኻከል ነው




የተደረጉት፥ ያም በጣም ሞቃቱ የሲያል ቦታ ነው። እንዲሁም ሂትለር (በጀርመን የናዚ መሪ የነበረ፣ ብዙ አይሁድንና ሌሎች ንጹኀንን በግፍ የጨፈጨፈ ...)፤ ስታሊን (በቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት ለብዙ አስር ሚሊዮኖች ስቃይና ሞት ምክንያት የነበረ አምባገነን መሪ ነበር። ...)፤ ማኦ ዜዶንግ (በቻይና የኮሚኒዝም መሪና የአሁኗ የቻይና ሪፐብሊክ መስራች ነበር...)፤ እናም በሰሜን ኮሪያ ታዋቂ የነበረ ስሙ መጋቢ ካንግ፣ እናም ዝነኛ የጃፓን ጀግና፣ እናም ብዙ ብዙዎችን አየሁ።

ከዚያም ድቅድቅ ጨለማ ወደሆነው ስፍራ ደረስን፥ እርምጃችሁን እንኳ ለማየት እስኪሳናችሁ ድረስ በጣም ጨለማ ነበር። "*መላእክት! መላእክት!* በጣም ጨለማ ነው! እንዴት የሆነ ነገር ላይ እችላለሁ?" ብዬ ጮኽኩ። *መላእክቱ* ትከሻዬን መታ መታ አድርገው "*ትንሽ ብቻ ጠብቅ።*" አሉኝ።

በጥቂት ደቂቆዎች ውስጥ፥ የማይቆጠሩ ሰዎችን እርቃናቸውን ሆነው ማየት ቻልሁ። ሁሉም መላ ሰውነታቸው በትሎች ተሸፍኗል። አንዳች የተተወ ቦታ በሰውነታቸው ላይ የለም፥ መላ ሰውነታቸው ሙሉ በሙሉ በትሎች ተሸፍኗል። እርቃናቸውን ያሉት ሰዎች ጥርሳቸውን እያፋጩ ትሎቹን ለማራገፍ ይሞክራሉ። "እነዚህ ሰዎች በምድር ሲኖሩ ምን አድርገው ነው?" ብዬ ጠየቅሁ።

"*እነዚህ እርስ በእርሳቸው ሲወቃቀሱና ሲተማሙ የነበሩ ሰዎች ናቸው። አንዳቸው ለአንዳቸው ስለሚናገሩት ነገር አይጠነቀቁም።*" (ማቴዎስ 5፥22)



አጋንንት ሰዎችን በማጭድ ሲበሳሷቸውና ሆዳቸውን ሲወጓቸው አየሁ። አጃቢዬን "*መላእክት፥*እነዚህ ሰዎች በምድር ሲኖሩ ያደረጉት ምንድ ነው?" ብዬ ጠየኳቸው።

"*እነዚህ ሰዎች ሥራ፣ ቤት፣ እና ቤተሰብ ነበሯቸው፥ ነገር ግን **ለእግዚአብሔር** አልሰጡም። ለድሀ፣ ለቤተክርስቲያናቸው፣ አሊያም ለሌሎች **አምላካዊ** ተግባሮች አልረዱም። በጣም ስስታምና ቋጣሪዎች ነበሩ። ድሀ እንኳ ቢያጋጥማቸው፥ አልፈውት ይሄዳሉ እንጂ ግድ የላቸውም። ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ብቻ ነው የሚጨነቁት። በአግባቡ ይለብሳሉ፣ ይበላሉ፣ እንዲሁም የተመቻቸ ህይወት ነበራቸው። ለዚህ ነው ሆዳቸው እየተበሳሳ ያለው ከርሳቸው በስስት ተሞልቷልና።*" (ምሳሌ 28፥27)

በጣም አስፈሪ እይታ ነበር። እነዚህን ክስተቶች ካየሁ በኋላ፥ ወደ ምድር ስመለስ፥ ያለኝን ገንዘብና ንብረት ሁሉ ለሌሎች ሰጠሁ። መዳን በገንዘብም ሆነ በንብረት አይገኝም። በእምነት እንጂ። ሲያል ሊቋቋሙት የማይቻልና የተቃወሰ ቦታ ነው። ዘላለማዊ ስቃይ ነው!



ራሳቸውን በጣም ስለታም በሆነ መሣሪያ የተቆረጡ ሰዎችንም አየሁ። *መላእክቱን* “እነዚህ ሰዎች እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ስቃይ የሚደርስባቸው ምን አድርገው ነው?” ብዬ ጠየቅሁት። *መልአኩም* መለሰ፥ “*መልካምና ጠቃሚ ነገሮችን እንዲያስቡ አዕምሮ በ**እግዚአብሔር** ተሰጥቷቸው ነበር። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች አስቀያሚ ነገሮችን ያስቡ ነበር። ሴሰኛ ነገርን ያስቡ ነበር።*” (ማቴዎስ 5፡28)

ቀጥሎ፥ ሰዎች ሲወጉና ሲቆራረጡ አየሁ። እይታው በጣም ዘግናኝ ነበር። “እነዚህስ ሰዎች? በዚህ መልኩ የሚሰቃዩት ምን አድርገው ነው?” ብዬ ጠየቅሁኝ። *መልአኩም* “*እነዚህ ቤተክርስቲያናቸውን ያላገለገሉ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ናቸው። እውነት ለመናገር፥ መሥራትም ሆነ ማገልገል አይፈልጉም! ይወዱት የነበረው ብቸኛው ነገር ከመንጋው መቀበል መቀበል ብቻ ነበር።*” (ዘካሪያስ 11፡17፤ ሆሴዕ 6፡5)



ሽማግሌዎችን፣ ዲያቆናትን እናም ሌሎች አማኞችን በአጋንንት ሲሰቃዩ አየሁ። አጋንንቱ በምላሳቸው ውስጥ ቀዳዳ አድርገው እርስ በእርሳቸው በገመድ ሲያይዟቸው አየሁ። ከዛም አጋንንቱ ሰዎቹን በገመዱ ይጎትቷቸዋል። ደግሜ ጠየቅሁ፥ “በምድር ምንድ ነው የሠሩት?” *መልአኩም መለሰ፥* “*እነዚህ ሦስት ዓይነት ኃጢአቶችን ሠርተዋል።*

*አንደኛው፥ መጋቢዎቻቸውን ወቅሰዋል።* ስለመጋቢዎቻቸው አሉታዊ ንግግርን ተናግረዋቸዋል። *መጋቢዎቻቸውን ያሙና ያሾፉባቸው* ነበር።” (ያዕቆብ 3፡6፤ ማቴዎስ 12፡37)

እንደዚህ ዓይነቱን *ሥራ* የሠራችሁ ሁሉ እለምናችኋለው **ንስሐ ግቡ፥ንሰሐ ግቡ**!!

*መልአኩ* ቀጠለ፥ “*ሁለተኛው፥ በቃላቸው ቤተክርስቲያኑን አቃለሉ። ጽኑዎች አማኞች እንኳ በእነርሱ ተጠቅተው ቤተክርስቲያን መምጣት እስኪተዉና አንዳንዶቹ ማመን እንኳ እስኪያቆሙ ድረስ ሌሎች ክርስቲያኖችን አወኩ። ታማኝ ክርስቲያኖች የ**እግዚአብሔርን** ሥራ እንዳይሠሩ የሚቻላቸውን ሁሉ አደረጉ። እነዚህ አመጸኞች ብዙ ታማኞች እንዲሰናከሉ አደረጉ። በመጨረሻም፥ ሰክረው የቤተሰብ አጋራቸውን የሚበድሉ የትዳር አጋሮችም አሉ።*”



አጋንንት ወንዶችንና ሴቶችን ሆዳቸውን በግዙፍ ሚስማሮች ሲወጓቸው አየሁ። “ምን አድርገው ነው?” ብዬ ጠየቅሁኝ። *መልአኩም* “*እነዚህ ሳይጋቡ አብረው ሲኖሩ የነበሩ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። እነዚህ በማርገዛቸው ጊዜ ውርጃ ስለፈጸሙም ጥፋተኞች ናቸው። ፈጽሞ ንስሐ አልገቡም።*” አለኝ።

ሌሎች ሰዎችንም አየሁ። አንድ ሰው በስሱ *ሥጋን* ወይም አታክልትን እንደሚሰነጥቅ አጋንንት ምላሶቻቸውን ይሰነጣጥቋቸው ነበር። “እነዚህ ሰዎች በዚህ መልኩ የሚሰቃዩት ምን አድርገው ነው?” ብዬ ጠየቅሁ። *መልአኩ* “*እነዚህ ለቤተሰቦቻቸው በኃይለቃል የሚመልሱ ልጆችና ምራቶች ናቸው። ነገሮችን ከማባባስ ፋንታ ሊሉ የሚገባቸው ነገር ‘ይቅርታ’ ማለት ብቻ ነበር። አብዛኞቹ ጸያፍ ቃላትን ተጠቅመዋል። ቤተሰቦቻቸውን በክፉ ቃላት አሳዝነዋል። አመጸኞች ነበሩ። ለዚህ ነው ምላሳቸው እየተሰነጣጠቀ ያለው።*” አለኝ።

ወንድሞች፥ ሁላችንም አንድ ቀን እንሞታለን፥ ነገር ግን ያ መቼ እንደሚሆን አናውቅም። እባካችሁ የተዘጋጃችሁ ሁኑ። መዘጋጀት ማለት ወደ ገነት መሄድ ማለት ነው። መቼ እንሄዳለን አይደለም ጥያቄው። እባካችሁ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ ይቅር ተባባሉ። ንስሐ ግቡ ንስሐ ግቡ እናም ማድረግ ካለባችሁ ሙሉ ቀኑን አድርጉት።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፥ እኔ እንደዚህ ዓይነት ምስክሮችን ቸል እል ነበር። እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ቸል የምል ግድ የለሽ ፕሬዝቢተሪያን መጋቢ ነበርሁ። አሁን ግን፥ ያየሁትን ነገር ለእናንተ መመስከር ይኖርብኛል። እባካችሁ ቅዱስ ህይወት ለመኖር እንዳታቅማሙ። እባካችሁ ይህን የተመሰቃቀል ስቃይና ፍርድ አስወገዱ። ዳኑ! ለሥጋችሁ አትኑሩ ነገር ግን **ለእግዚአብሔር** መንግሥት ተገዙ። እባካችሁ **ኢየሱስን** ለማያውቁት ጸልዩላቸው። ስበኩ ፍሬም አፍሩ። እባካችሁ ጠዋት በማለዳ ጸልዩ እሁድንም ቀድሱ። እባካችሁ በአግባቡ አስራታችሁን ለጌታ አቅርቡ። ሽልማታችሁን በሰማይ እንጂ በምድር አታከማቹ። በሁሉንቻዩ **በኢየሱስ** ስም እጸልያለሁ እባርካችሁም አለሁ!



በ መጋቢ ፓርክ፥ዮንግ ጊዩ

ቶማስም፦ ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው።
ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።
እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው። (የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል** በዮሐንስ 14:5-7)

እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፤

በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።
እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።
በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል።
በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።
ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል።
አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ።
እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። (የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል** በዮሐንስ 15:1-10)

[የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱስ ወንጌል በማቴዎስ 7:13-27 (The Gospel of **JESUS CHRIST** of Nazareth our Lord and Savior according to Matthew 7:13-27)

በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤

ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።

የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።

ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?

እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል።

መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም።

መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።

ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።

በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።

የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።

ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።

ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።

ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል።

ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።

የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱስ ወንጌል በዮሐንስ 3:5-6 (The Gospel of **JESUS CHRIST** of Nazareth our Lord and Savior according to John 3:5-6)

ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።

ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።

የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱስ ወንጌል በዮሐንስ 3:16-21 (The Gospel of **JESUS CHRIST** of Nazareth our Lord and Savior according to John 3:16-21)

ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።
ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።
የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥
መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥
መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።
እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።
የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።
በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ።
እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ። (ወደ ገላትያ ሰዎች 5:16-26) (Galatians 5:16-26)

በዙፋንም የተቀመጠው፡- እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ።

አለኝም፡- ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ።

ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።

ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።] (የዮሐንስ ራእይ 21:5-8) (Revelation 21:5-8)

**በታላቅም ድምፅ እየጮሁ:- በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።**
**መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ:-**
**አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።** (የዮሐንስ ራእይ 7:10-12)

**በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።**
**ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ**
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com